# ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

## በቱሪዝም ዘርፍ ለሚሰማሩ የውጭ ሀገር

## ባለሙያዎች ቅጥር ድጋፍ አሠጣጥ

## መመሪያ ቁጥር475/2013

ነሐሴ 2008 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# መመሪያ ቁጥር 475/2013

## በቱሪዝም ዘርፍ ስለሚሰማሩ የውጭ ሀገር ባለሙያዎች ቅጥር ድጋፍ አሠጣጥ የወጣ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር መመሪያ

መንግስት በፈጠረው ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ የሀገራችንና የውጭ ባለሀብቶች በቱሪዝም ዘርፍ የሚያደርጉት ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ደረጃ በመስፋፋት ላይ የሚገኝ ከመሆኑ የተነሳ፣ በሆቴል፣ ሬስቶራንት፣ ሎጅና አስጎብኚ ድርጅት የንግድ ዘርፎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ባለሀብቶች መሰማራታቸውን ተከትሎ የሀገር ውስጥ ባለሙያዎች እጥረት በመስተዋሉ፣

የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች በተለያዩ የሥራ መስኮች ቀጥረው ለማሰራት የሚፈልጓቸው የውጭ ባለሙያዎች የዜጎችን የሥራ ዕድል የማይሻማ መሆኑን በማረጋገጥ፣ ከፍተኛ ክህሎት እና ልምድ ያላቸው የውጭ ባለሙያዎች በተመረጡ የሙያ መስኮች እንዲሰማሩ ትብብር በማድረግ ያላቸውን ዕውቀትና ክህሎት ለዜጎች እንዲያስተላልፉ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ለተገልጋዮች ግልጽ፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ተጠያቂነት ያለበት የአሠራር ሥርዓት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀፅ 35 የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመፈፀም እንዲያስችል ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "በቱሪዝም ዘርፍ ለሚሰማሩ የውጭ ሀገር ባለሙያዎች ቅጥር ድጋፍ አሠጣጥ መመሪያ ቁጥር 475/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "ድጋፍ" ማለት ማንኛውም የውጭ ሀገር ባለሙያ በሀገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ በሚንቀሳቀሱ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥሮ ለመሥራት እንዲያስችለው ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የሚፃፍ የድጋፍ ደብዳቤ ነው፡፡
2) "ድርጅት" ማለት የሆቴል፣ ሎጅ፣ ሞቴል፣ ሪዞርት፣ ሬስቶራንት፣ አስጎብኚ፣ የሆቴልና ቱሪዝም ማማከር አገልግሎት፣ ልዩ ዝግጅት የማስተባበር፣ ቱሪዝም ፕሮሞሽን ሥራዎችን የሚያከናውን የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ነው፡፡
3) "ማኔጅመንት ኮንትራክት" ማለት በቱሪዝም ዘርፍ የአንድ ድርጅት የሥራ አመራር ተግባራት በሌላ ድርጅት እንዲከናወን የሚፈፀም የስምምነት ውል ነው፡፡
4) "ሥራ አስኪያጅ" ማለት በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማራን ድርጅት በበላይነት የሚያስተዳድር ሰው ነው፡፡
5) "የሥራ ክፍል ኃላፊ" ማለት በሆቴል፣ በሬስቶራንት፣ በሎጅና አስጎብኝ ድርጅት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የሥራ ክፍሎችን የሚመራ ሰው ነው፡፡
6) "ሙያ" ማለት የቱሪዝም አገልግሎትን ጥራትና ብቃት ባለው መልክ ለመስጠት የሚያስችል ዕውቀትና ክህሎት ነው፡፡
7) "ሚኒስቴር" ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፣
8) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
9) በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዓላማ

1) በቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የሚቀጠሩ የውጭ ሀገር ባለሙያዎች ድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓት ግልፅ፣ ተዓማኒነትና ወጥነት ያለው እንዲሆን ማድረግ፤
2) የውጭ ሀገር ባለሙያዎች ያላቸውን ዕውቀትና ክህሎት ለኢትዮጵያዊያን የሚያስተላልፉበት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በዘርፉ የሚታየውን የቴክኖሎጂ፣ ዕውቀት እና ክህሎት ክፍተት ለመሙላት እገዛ ማድረግ፣

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የውጭ ሀገር ባለሙያዎችን በሚቀጥር በማንኛውም የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>
# <u>ስለድጋፍ አሰጣጥ</u>

5. <u>መሠረት</u>

ማንኛውም የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የውጭ ሀገር ባለሙያዎችን ቀጥሮ ለማሠራት ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ለማግኘት በቅድሚያ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የድጋፍ ድብዳቤ ማግኘት አለበት፡፡

6. <u>የድጋፍ ደብዳቤ የሚጻፍላቸው የሙያ ዓይነቶች</u>

1) የድጋፍ ደብዳቤ የሚጻፈው በሚከተሉት የሙያ ዓይነቶች ብቻ ይሆናል፡፡
   ሀ) በምግብ ዝግጅት ሙያ ከባለአንድ እስከ ባለአምስት ኮከብ ሆቴል፣ ለአየር መንገዶች ምግብ በማቅረብ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች፣ ሬስቶራንት፣ ሎጅ እና ሞቴል በሙያተኝነት

ለ) በባለ ሦስት እና ከዚያ በላይ ኮከብ ሆቴል ፣ ለአየር መንገዶች በምግብ ማቅረብ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች፣ ሬስቶራንት፣ ሎጅ፣ ሞቴል ፣ በሥራ አስኪያጅነትና በሥራ ክፍል ኃላፊነት፣

ሐ) የቱሪዝምን ፍሰት ለማሳደግ ዕውቅና ባላቸው አስጎብኚ ድርጅቶች ለሚከናወን የውጭ ገበያ በማፈላለግ /ማርኬቲንግ/ ሥራ በባለሙያነት፡፡

2) ዓለም አቀፍ ንግድ ምልክት (ብራንድ) ያላቸው ሆቴሎች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 (ሀ) እና (ለ) በተጠቀሱት የሙያ ዓይነቶች እና በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት እንዳስፈላጊነቱ በሌሎች ተያያዥ የሙያ አይነቶች ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

## 7. <u>የድጋፍ አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታዎች</u>

ማንኛውም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የድጋፍ ደብዳቤ እንዲፃፍለት ሲጠይቅ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፤

1) የተቀጣሪው የውጭ ሀገር ዜጋ ስም፣ ዜግነት፣ የቅጥር ውል፣ የሚቀጠርበት የሥራ መደብ መጠሪያ ማስረጃ እና የታደሰ የፓስፖርት ኮፒ፤

2) አብሮ የሚሠራው ተተኪ ኢትዮጵያዊ ባልደረባ ስም፣ የትምህርትና የሥራ ልምድ፤

3) የተቀጣሪው የውጭ ሀገር ባለሙያ የሥራ ልምድ ማሥረጃ፤

4) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6(ለ) መሰረት በሥራ አስኪያጅነት ለሚቀጠሩ የውጪ ሀገር ዜጎች በሆቴል/ሆስፒታሊቲ አስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም አግባብነት ያለው ቢያንስ 6 ዓመት የሥራ ልምድ ማስረጃ፤

5) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6(ለ) መሰረት በሥራ ክፍል ኃላፊነት በሚሰማሩበት የሥራ መደብ የመጀመሪያ ዲግሪ እና ቢያንስ 4 ዓመት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ፤

6) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6(ሀ) ወይም 6(ሐ) መሰረት በሙያተኝነት ለሚቀጠሩ በሚሰሩበት የሥራ መደብ ዲፕሎማ እና አግባብነት ያለው ቢያንስ 3 ዓመት የሥራ ልምድ፤

7) ቅጥሩ ለተጠየቀለት የሥራ መደብ በድርጅቱ ተቀጥረው ከሚሠሩ ሠራተኞች መካከል ለማሳደግ አለመቻሉን የሚገልፅ የውስጥ ማስታወቂያ ወይም ከድርጅቱ ውጪ ኢትዮጵያውያን አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር አለመቻሉን የሚያመላክት የውጭ ማስታወቂያ፡፡

8. <u>ማስረጃዎችን ስለማረጋገጥ</u>

ሀ) ማንኛውም የውጭ ዜጋ የሚያቀርበዉ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ አግባብነት ሀገሩ ባለ በሚመለከተው መንግስታዊ አካል የተረጋገጠ መሆን ይኖርታል፤

ለ) ተቀጣሪው የውጪ ሀገር ዜጋ የትምህርት እና የሥራ ልምድ ማስረጃዎቹን ከሚኖርበት ሀገር ትክክለኛነቱን ሳያረጋግጥ ወደ ሀገር ከገባ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ በተማረበት ወይም በሠራበት ሀገር ኤምባሲ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

9. <u>ስለድጋፍ ጥያቄ አቀራረብ</u>

1) ማንኛውም ሰው ወይም የውጭ ዜጋ የቅጥር ድጋፍ ጥያቄ ሲያቀርብ ሚኒስቴሩ የሚያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ እና የቱሪዝም ስነ-ምግባር መመሪያውን ተግባራዊ እንደሚያደርግ ግዴታ የሚገባበትን ቅፅ በመሙላት፤ አስፈላጊ መረጃዎችንና ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት በአካል ወይም በህጋዊ ወኪሉ አማካኝነት ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፤
2) ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ በተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች መሰረት የቀረበውን ጥያቄ ገምግሞ ውጤቱን በአንድ ቀን (8 ሰዓት) ውስጥ ያሳውቃል፡፡
3) ለግምገማ የቀረበው ማመልከቻ ቅድመ ሁኔታዎችን ወይም አስፈላጊ መረጃዎችን የማያሟላ ሆኖ ከተገኘ ጥያቄውን ላቀረበው አካል አሟልቶ ወይም አስተካክሎ እንዲያቀርብ ይገለጽለታል፡፡

10. <u>ስለዕድሳት</u>

1) የውጭ ሀገር ባለሙያ እንዲቀጠር የተጻፈ የድጋፍ ደብዳቤ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለውጭ ሀገር ዜጋ ቅጥር የዕድሳት ደብዳቤ የሚጻፈው

   ሀ. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ለተከናወነ የውጭ ሀገር ዜጋ ቅጥር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ፤

ለ. የቅጥር ዕድሳት ለተጠየቀለት የሥራ መደብ የውጭ ሀገር ዜጋው ከሥራው ጐን ለጐን ኢትዮጵያውያንን በማሰልጠን ለመተካት ያደረገውን ጥረት የሚገልጽ አጭር ሪፖርት ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

3) ለአንድ የውጭ ሀገር ዜጋ የሥራ ፈቃድ እድሳት የሚደረገው አግባብነት ባለው ህግ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ብቻ ይሆናል፡፡

4) ዓለም አቀፍ ብራንድ ባላቸው ድርጅቶች የሚተዳደሩ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ አይመለከታቸውም፡፡

11. <u>ክትትል እና መረጃ አያያዝ</u>

ሚኒስቴሩ ፈቃድ እንዲሰጣቸው የድጋፍ ደብዳቤ የተፃፈላቸውን ባለሙያዎች አስመልክቶ መረጃ ያደራጃል፣ እንዳስፈላጊነቱም በተሰጣቸው ፈቃድና በሀገሪቱ ህጎች መሠረት እየሠሩ ስለመሆኑ ክትትል ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

12. <u>ልዩ ልዩ</u>

1) ማንኛውም የድጋፍ ደብዳቤ ተጽፎለት የውጭ ሀገር ዜጋን ቀጥሮ ሲያሠራ የነበረ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት የፈቃድ ዘመኑ በመጠናቀቁ ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት የሥራ ውሉ ቢቋረጥ ሁኔታውን በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

2) ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ የተከናወነ የውጭ ሀገር ዜጋ ቅጥር በዚህ መመሪያ መሠረት መታደስ አለበት፡፡

13. <u>የቅሬታ አቀራረብ</u>

1) በድጋፍ አሰጣጥ ሂደት ላይ ቅሬታ ያለው አካል ቅሬታውን ጉዳዩ በተፈፀመ በ15 /አሥራ አምስት/ የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለሚኒስቴሩ የተገልጋዮች ቅሬታ ማስተናገጃ ክፍል ማቅረብ ይችላል፡፡

2) የተገልጋዮች ቅሬታ ማስተናገጃ ክፍሉ ጥያቄው በቀረበ በ 5 /አምስት/ የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

3) በቅሬታ ማስተናገጃ ክፍሉ ምላሽ ያልረካ ተገልጋይ አቤቱታውን በ10 /አሥር/ የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል፡፡
4) ሚኒስቴሩ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔውን በ5 /አምስት/ የሥራ ቀናት ያሳውቃል፤ የሚኒስቴሩ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

14. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም የሚመለከተው ሰው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

15. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

16. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

<u>አዲስ አበባ ነሐሴ 13 ቀን 2008 ዓ.ም.</u>